# ነገረ ሚዲያ ዘ ኢትዮጵያ፡ጋዜጠኝነት ወይስ “አክቲቪዝም”?


መኮንን አማረ

09-14-14

Meklle University

Journalism & Communications Dept.

mekonnenam@yahoo.com


አገራችን ኢትዮጲያን ጨምሮ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በቅጡ ባልዳበረባቸው አገራት ዉስጥ ምክንያታዊና አሳታፊ ሚዲያን መፍጠር ፈተናዉ የበዛ ነው ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን የመገዳደር ያህል ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።ባጭር ቋንቋ ለማስቀመጥ ያህል የምክንያታዊና አሳታፊ ሚዲያ ውልደትና ህልውና የተመሰረተው በተፈጥሮ አባቱ፦ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕውን የመሆኑን ሃቅ ለመረዳት በአንፃራዊ መልኩ በበርካታ የአለማችን ክፍሎች የተስተዋለውና ላለፉት 60 ና 70 ዓመታት የዘለቀውን የ‘ዴሞክራሲያዊ ሚዲያ’ የዕድገት ታሪክ መመልከት ይረዳል።

የምክንያታዊና አሳታፊ ሚዲያ ባህል በዳበረባቸው ሃገራት ዉስጥ ጋዜጠኝነትና “አክቲቪዝም” በሁለት የተለያየ ጎራዎች የሚንቀሳቀሱ የሞያ ዘርፎች ሲሆኑ በአንፃሩ የ‘ዴሞክራሲያዊ ሚዲያ’አላባውያን ባልተሟሉባቸው አገራት ዘንድ እነዚህ ሁለት የሞያ ዘርፎች አንዱ ሌላዉን ተክቶ የሚሰራበት ሁኔታ በእጅጉ የበዛ ነው። በኢትዮጲያችንም እየተስተዋለ ያለው የሚዲያ እንቅስቃሴ ጋዜጠኝነትንና “አክቲቪዝም”ን በአንድና በተመሳሳይ የመጫወቻ ማልያ የሚመለከት ይመስላል።

አሁን አሁን በተጨባጭ እንደምናየው ጋዜጠኝነትንና “አክቲቪዝም”ን በደምሳሳው በአንድ ጆንያ ከቶ አንድና ያው እንደሆኑ የመመልከቱ ቅኝት በሁለቱ ሞያዎች መካከል ያለዉን ሰፊ መስመር መገንዘብ ያለመቻል አልያም የመረዳት ፍላጎቱ ፈጽሞ ያለመኖር እውነታን ያሳብቃል።

እውነታው ግን የጋዜጠኝነትና “አክቲቪዝም” ሞያዎች ከሚገናኙበት ቀጭን ገመድ በዘለለ በመርሕ፣ በዓላማና በአተገባበር ለየቅል ሆነው እናገኛቸዋለን።በሁለቱ የሞያ ዘርፎች መሃል ያለውን ክፍተት ለማንጠር ያህል እስቲ አሁን ደግሞ የእያንዳንዳቸዉን ምንነት፣ የቆሙለትን መርሕ እንዲሁም አተገባበር ለመፈተሽ እንሞክር።

ጋዜጠኝነት በመሠረታዊ ጽንሰ ሓሳቡ መረጃን በማደን፣ በመሰብሰብ፣በማዋቀርና በማንጠር እንዲሁም በመዘርጋትና በማከፋፈል በሕብረተሰቡና በዴሞክራሲያዊ ምርጫና በሕግ ማዕቀፍ በሚሠራ መንግሥት መካከል ባለው የኃላፊነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና የሕግ የበላይነት መስተጋበር ውስጥ የሚንቀሳቀስ የሞያ ዘርፍ ነው። በሌላ መልኩ “አክቲቪዝም” በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን ሥር የተማከለን ማሕበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ስሜትን፣ አመለካከትን ብሎም ጥቅምን ለማስፈፀም በሚደረግ የለውጥ ግብ (ሥርነቀል አልያም አዝጋሚ) የተሰለፈ ሆኖ ለዚህ ለውጥ እውን መሆን አውዱና ግብዓቱ በሚፈቅደው መጠን አስቀድሞ የታሰበ የሕብረተሰብ ክፍልን በማንቃትና በማደራጀት ሥራ የሚጠመድ የሞያ ዘርፍ ነው።

ከሁለቱ ሞያዎች መሠረታዊ ምንነት የምንረዳው ነገር ቢኖር ጋዜጠኝነትና “አክቲቪዝም” ሕብረተሰቡን በማሰተማርና በማንቃት ረገድ የሚጋሩት ቀጭን መስመር ቢኖርም በጋዜጠኝነት ሞያ ዉስጥ ግድ የሚሉ እሴቶች ማለትም ተጠያቂነት፣ አሳታፊነት፣ ዕውቀትንና ክህሎትን በኃላፊነት የመከወንና በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የመንቀሳቀስ ሁነቶች በአክቲቪዝም ሞያ ውስጥ ችላ የሚባሉበት አጋጣሚዎች የበዙ ናቸው። አዚህ ላይ በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን እንዲሁም ሞያው በሚጠይቀው ሥነምግባር ዙርያ በርካታ የጥናትና የምርምር ውጤቶችን ያበረከቱት ፕሮፌሰር ቦብ ስቲልን መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል።ፕሮፌሰር ቦብ ስቲል በጋዜጠኛና በአክቲቪስት ያለዉን ልዩነት እንዲህ ይገልጹታል፦

“An activist is someone who pushes a cause without aiming to reflect an alternative viewpoint,--- one who makes no attempt to remain objective and impartial while a journalist must always aim to avoid becoming emotionally and politically involved in the issues he/she is covering.”

ይህን ሃሳብ ወደ አማርኛ ስንመልሰው "አክቲቪስት ማለት የትግል መነሻን ዉጤታማ ለማድረግ በሚደረግ ሂደት ውስጥ ሌሎች አማራጭ አመለካከቶችን ለማስተናገድ የማያስብና ምክንያታዊና ገለልተኛ ለመሆን የማይጥር ሲሆን ጋዜጠኛው በአንፃሩ የራሱን ግላዊና ፖለቲካዊ ስሜት ከሚዘግበው ዘገባ ማራቅ ይጠበቅበታል።" የሚል መልዕክት ይኖረዋል።

በሁለቱም ሞያዎች መሓል ይህን ያህል ሰፊ ልዩነት የመኖሩን እዉነታ ስናስብ የዴሞክራሲ ሥርዓት ባልዳበረባቸው እንደ ኢትዮጲያ ባሉ አገራት ዘንድ ሞያዎቹን አንድ ላይ የማስኬዱ ሂደት ምን ያህል በውስብስብ ተግዳሮቶች የታጀበ ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ቀላል ነው። ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያትም የአክቲቪዝም መሠረታዊ መገለጫዎች የሚያጠነጥኑት በማናቸውም መንገድ ማለትም አቅሙና ሁኔታው በፈቀደው መጠን ለውጥን በአጭር ወቅት ካልተሳካም በተራዘመ ጊዜ ዉስጥ እውን ማድረግን ታሳቢ ያደረገ እንደመሆኑ ፈረንጆች " whatever it takes!" በሚሉት ፈሊጥ የተቃኙ አቋራጭ መድረኮች የሞያው መትከሎች ሆነው የሚያገለግሉበት እድል ሰፊ ነው።

ይህን ካየን ዘንዳ ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ቁልፍ ጥያቄ ቢኖር ኸረ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የመንግስትም ሆነ የግል የሚዲያ ተቋማት ዘንድ ከጋዜጠኝነትና "አክቲቪዝም" የትኛው ገዝፎ ይስተዋላል የሚለው ይሆናል። በተያያዥ ቅኝትም አገሪቱ ዉስጥ ያለውን የሚዲያ ሁነት መሠረታዊ ባህሪያት፣ እየታዩ ያሉ ችግሮች፣ መንስዔዎቻቸውንና የመፍትሄ አቅጣጫዎቹን ማቅረቡ ግድ ይላል።

የፖለቲካ ባህላችን፡-

ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለው የባህል ታሪካችን በውስብስብና ኋላቀር አመለካከቶች የተሞላ መሆኑ የአገራችንን የፖለቲካ ባህል በእጅጉ አቀጭጮታል። የፖለቲካ ባህላችን ጉልበተኛንና አሸናፊን የዉዳሴ ከንቱን በመለገስና የጀግናን አክሊል በመሸለም ይታወቃል። ከተመሳሳይ ፖለቲካዊ ባህል በሚቀዳው አመለካከት ምክንያትም ጉልበተኛው አልያም አሸናፊው የጨዎታዉን ሕግ በበላይነት ይቆጣጠራል እንዳስፈላጊነቱም የጨዎታዉን ሕግ በራሱ ዛቢያ የመምራት ሥልጣን ይኖረዋል ።በቀላሉ ላስተዋለ ይህን መሰሉ ትዕይንት ልጆች እያለን በምንዝናናባቸው የልጆች ጨዋታዎች በዕድሜ ወይም

በጉልበት የሚበልጠን ልጅ የጨዎታዉን ሕግ እንዳሻው ሲዘዉረው ጉልቤው ተፈጥሮአዊና ሞራላዊ ልዕልና እንዳለው እያሰብን ያደግንባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው።

ለዚህም ይመስላል ያላደግንበትንና ያልለመደብንን የባህል ዕሴት ማለትም መብትን ሰላማዊ በሆነ መልኩ የመጠየቅና ጉልበተኛውም ጭምር እንዲያከብረው የማድረግ የፖለቲካ አመለካከት ማጎልበት አሁንም አቀበት እንደሆነብን የዘለቀው። የዚሁ ባህላችን መገለጫዎች ሆነው የዘለቁት ፖለቲካዊ ዕሴቶች የሚያመዝኑት ከዉይይት ይልቅ ክርክር፣ ከድርድር ይልቅ ነፍጥ እንዲሁም ከምክንያታዊነት ይልቅ ስሜታዊነት ያጠላባቸው ናቸው።

ምክንያታዊና አሳታፊ ሚዲያ ከመፍጠር አንጻር ኋላቀሩ የፖለቲካ ባህላችን ያስከተለዉን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመረዳት  አገራችን ዉስጥ ያሉት አብዛኞቹ የፕሬስ ውጤቶች እያራመዱ ያሉትን ፅንፍ የያዙ አመለካከቶችን ማየቱ ብቻ በቂ ይሆናል። በሃገራችን ፖለቲካዊ ባህል ዉስጥ የመሃል መንገድ አመለካከቶች (attempts to strike middle ground) ቦታ የላቸውም፤ ፈረንጆቹ either you are black or white የሚሉት አይነት፦ በሃበሻ ምድር የመሃል መንገድ አመለካከት የሚያቀነቅን ግለስብ አልያም ቡድን "ወላዋይ" ወይንም "አቋም የለሽ" አይነት ታርጋዎች ይለጠፍበታል-----በሌላ መልኩ ወይ የገዢው ፓርቲ አልያም የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ መሆን ይጠበቅብሃል እንደማለት ነው። ዕውቁ የፖለቲካል ሳይንቲስት ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ አወዛጋቢውን የ1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ የተፈጠሩ ፅንፍ የያዙ አመለካከቶችን የታዘቡ ጊዜ ያሉት ይህን ነበር "ኢትዮጲያ ዉስጥ ገለልተኛ አመለካከት ያለው እንደ ከሃዲ ይቆጠራል በመሆኑም አገራችን ውስጥ ገለልተኛ መሆን የሚቻለው ዘፈን ላይ ብቻ ይመስለኛል" በማለት የበዛወርቅ አስፋውን የትዝታ ዘፈን የጠቀሱበት አጋጣሚ ትዝ ይለኛል፦

> የማነሽ ይሉኛል የማን ልበላቸው፣
> ብችየን ብቆይስ ምን አስጨነቃቸው።
> አይቻልም ወይ መኖር የማንም ሳይሆኑ-----

ፅንፍ የያዙ አመለካከቶችን ከመፍጠር ባሻገር ኋላቀሩ የፖለተካ ባህላችን በጋዜጠኝነት ሞያ ላይ ያስከተለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመገንዘብ በአብዛኞቹ የሕትመት ዉጤቶች

የሚዘወተረዉን የቋንቋ ምርጫና የቃላት አጠቃቀም መመልከት ይቻላል። ዴሞክራሲያዊ የሃሳብ ግብይት በመሠረታዊ ባህሪው መለሳለስና የቃላት በጎነት ይጠይቃል። ነገር ግን እንደ አለመታደል ሆኖ በአብዛኞቹ የሕትመት ዉጤቶቻችን (በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ) ዘንድ የሚስተዋለው የቋንቋ ምርጫና የቃላት አጠቃቀም ቂም በቀልን ያዘለ፣ ስድብ የተጠናወተውና ቀረርቶ አልያም ኩርፊያን የሚያስተጋባ ነው። ጥቂቶቹን በዋቢነት ለመጥቀስ ያህል፡- "መንግስት" ከማለት ፈንታ "ገዢው ስብስብ"፣ "የኔን ሃሳብ የማይቀበል" እንደማለት "አድሃሪ" የሚሉት ይገኙባቸዋል። ይህ ደግሞ የሃሳብ ግብይት ባህልን ከማዳበርና የውይይትና የድርድር መድረኮችን ከመፍጠር አንጻር መንገዱን ዝግ የሚያደርግ ሆኖ እናገኘዋለን።

ስለዚህ በተያያዥ የትንታኔ ምልከታ ጋዜጠኞች እንደማንኛውም አካል ማለትም ( መንግስት፣ ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወዘተ) ማሕበረሰቡ ዉስጥ ጎልቶ ከሚታየው የፖለቲካ ባህል የተቀዱ እንደመሆናቸው ከተለመደው የአመለካከትና የቅኝት ማዕቀፍ ውጭ የመሆናቸው ዕድል በብዙ ፈተናዎች የተሞላ ነው። በመሆኑም አገራችን ውስጥ ያሉት አብዛኖቹ የሕትመት ውጤቶች ፅንፍ በያዙ ሁለት ጎራዎች ተቸክለው የቀሩ ይመስላሉ። ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ ያስተዋልነዉ ነገር ቢኖር አንዱ ጫፍ እጅ እጅ በሚል ፕሮፖጋንዳ ዉስጥ ሲዳክር ሌላዉ ጫፍ ደግሞ የሀገርንና የህዝብን ጥቅም ግምት ዉስጥ ባላስገባ ወሰንየለሽ ተቃዉሞ መጠመዱን ነው።

### የመንግስት ሚዲያ

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በወጉ ስር ባልሰደደባቸው አገራት ዘንድ መንግስት በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው የሚዲያ ተቋማት አሳታፊና ምክንያታዊ የመሆን ተስፋቸው የመነመነ ነው። ለዚህም ዋነኛ መከራከርያ ነጥብ ሆኖ የሚቀርበው ምክንያት በነዚህ አገራት ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ የዴሞክራሲ ተቋማት ሚዲያን ጨምሮ ተቋማዊ ነፃነትን ማረጋገጥ የተሳናቸው የመሆናቸው እውነት ነው። አገራችን ዉስጥ እንደምናየውም ተቋማዊ ነፃነት ባልጎለበተበት ሁኔታ የመንግስት ሚዲያን ወደ ሕዝብ አገልጋይ የሚዲያ ተቋም የማሸጋገሩ ሁነት አመክኖአዊ ባለመሆኑ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱን ፈታኝ ያደርገዋል።

በ1991 እ.አ.አ ዩኔስኮ ባዘጋጀው ዓለማቀፋዊ የፐሬስ ኮንፈረንስ ላይ የዩኒቨርሲቲ ኦፍ ጋና፣ ስኩል ኦፍ ኮሚዩኒኬሽን ሰተዲስ ዳይረክተር የሆኑት ፖል አናሽ የአፍሪካን ሚዲያ አስመልክቶ ባቀረቡት የጥናት ስራ አፍሪካ ዉስጥ በመንግስት ስር የሚንቀሳቀሱ አብዛኞቹ የመንግስት ሚዲያ ተቋማት የገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ ማሽኖች የመሆናቸዉን እውነታ አስምረዉበታል።

አገራችን ዉስጥ ያለው እውነታም ከዚህ የራቀ አይደለም። እንደውም ኢትዮጵያን ጨምሮ በበርካታ የአፍሪካ፣ኤስያና ላቲን አሜሪካ ሃገራት ዉስጥ በሚሰሩ የመንግስት ሚዲያ ተቋማት ዘንድ የሚታየው የሚዲያ ሁነት በቅርፅም ሆነ በይዘት ፈረንጆቹ፤ The Virtual Triangle- የሚሉት አይነት ይመስላል፤ በመንግስት ሚዲያ አደረጃጀት ዉስጥ ሕዝብን፣ መንግስትንና ገዢዉን ፓርቲ አንድና ያው አድርጎ የማየት ዝንባሌ የመፍጠር ሁነት እንደማለት ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ሌላው አብይ ጉዳይ ቢኖር የመንግስት ሚዲያ እንደ አራተኛ የመንግስት አካል ማለትም (ከሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ) ቀጥሎ በዴሞክራሲ ምርጫ የተመረጠን መንግስት የሕዝብ አገልጋይነቱንና በሕግ ማዕቀፍ ዉስጥ መንቀሳቀሱን የመቆጣጠር (government watchdog) ሚና ይወጣል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው።

ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለው ሌላው ችግር መንግስት አገሪቱ ውስጥ ሊኖር የሚገባ የሚዲያ ቅኝትና ይዘትን በተመለከተ አቋም የወሰደባቸውን የርዕዮተዓለማዊ መትከሎችና የሞያው አተገባበር አቅጣጫዎች ከፓርቲው ልሳናት በዘለለ የመንግስት ሚዲያን ጨምሮ ሌሎች የግል ሚዲያ ተቋማትም ካለምንም ማመቻመች ሊከተሏቸውና ሊተገብሯቸው የሚገባ ቀኖናዎች መሆን አለባቸው ብሎ የማመኑ ሁነት ነው። የጋዜጠኝነት ሞያ በመርሕ ከሚከተለው እውነታ አንፃር ማንኛውም የሚዲያ ተቋም ሃገሪቱ ውስጥ ያለውን የጫዎታ ሕግን እስካከበረና በዘገባው ምክንያታዊና ሚዛናዊ ለመሆን እስከጣረ ድረስ የሚያምንበትን ፖለቲካዊ አቋም የማራመድ ነፃነት እንዳለው ቢታመንም (ለምሳሌ ያህልም የእንግሊዙ ዘ ጋርዲያን ጋዜጣ በፖለቲካ አቋሙ ግራ-ዘመም ሲሆን የአሜሪካው ኒውዮርክ ታይምስ ቀኝ-ዘመም መሆኑን ልብ ይሏል!) በአንፃሩ በአገራችን የሚቀነቀነው የመንግስት አቋም ግን ይህንን የሞያው ነፃነት ፉርሽ ያደረገ ይመስላል።

እኛ አገር ዉስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታ መንግስት አገሪቱ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ የሚዲያ ተቋማት ህልውናቸው ቀጣይነት የሚኖረው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የቅኝት ምልከታና በልማታዊ ዴሞክራሲ የአተገባበር አቅጣጫ የሚዛን ልኬቱን ካሟሉ ብቻ ነው የሚለው አቋሙ ከሞያዉ መሠረታዊ ባህሪያት ጋር የሚላተም ሆኖ እናገኘዋለን። የጋራ መግባባትና ገዢ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮት በሌሉበት ሁኔታ የኔን የሃሳብ መንገድ ብቻ አቀንቅኑ የሚለው የመንግስት አቋም ዞሮ ዞሮ ከነችግሮቻቸው ጋዜጠኝነትን እየሞከሩ ያሉ ወገኖችን ፖለቲካዊ "አክቲቪዝም"ን እንዲቀላቀሉ ገፊ ምክንያት ሊሆን ይችላል።ይህ አቋም በቀላል ቋንቋ ሲሸረፍም መንግስት "ለየት ላሉ አመለካከቶች ቦታ የለኝም" እያለን ይመስላል። ይህ በራሱ ኢትዮጵያን ለመሰለ በተለያዩ የሕዝበች የስብጥር ቀለም ለምትታወቅ ሰፊ ሀገር ቀርቶ አንድ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ የአንድ ቤተሰብ አባላት ራሱ የሚመጥን እይታ አይደለም።

**የግሉ ሚዲያ፦**

ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የግል ሚዲያ ተቋማት ዘንድ ለሚስተዋለው ችግር መንግስት የራሱን ድርሻ ቢወስድም (ሞያው በሚጠይቀው ነፃነት ላይ ተገቢ ያልሆነ ገደብ በመጣል ረገድ) በአንፃሩ የግሉን ዘርፍ በተናጠልና ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ተጠያቂ የሚያደርጉ ጎልተው የወጡ ችግሮች ይታያሉ። እንደኔ እንደኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የግል ሚዲያ ዘርፍ መልክ በሦስት መሠረታዊ ችግሮች የታጀበ ነው።

በግሉ ሚዲያ ዘርፍ የሚስተዋለው የመጀመሪያው መሠረታዊ ችግር አገሪቱ ውስጥ ላለው መንግስት ሕጋዊ ዕውቅና (legitimacy) ካለመስጠት ይመነጫል። በአብዛኞቹ የግል ሚዲያ ተቋማት ዘንድ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግስት ሕጋዊ አካል ሳይሆን አገሪቱን በጫካ ሕግ የሚያስተዳድር የሽፍታ ቡድን ተደርጎ ይወሰዳል። በዚህ አረዳድም "ሕጋዊ መንግስት በሌለበት ሁኔታ አገሪቱ ውስጥ ያሉትን ሕጎች የማክበር ግዴታ የለብንም" የሚል አቋም የያዙ ይመስላሉ። ለዚህም ይመስላል ይህን መሰል የሕግና የሞራል ስነልቦና በያዙ የግል

ሚዲያ ተቋማት ዘንድ ጋዜጠኝነት ከሕግ ማዕቀፍ ውጭ የሚሠራ ልጓም አልባ የሞያ ዘርፍ እንደሆነ እየተቆጠረ ያለው።

ይህን የሕግና የሞራል እሳቤ መነሻ በማድረግም ዘርፉ በተጨባጭ እየሠራበት ያለዉን የሞያ አተገባበር አውድ ስንመለከት ሁነቱ ከጋዜጠኝነት ይልቅ ለፖለቲካል አክቲቨዝም በእጅጉ የቀረበ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህም ነው አብዛኞቹ የግል የሕትመት ውጤቶች ከምክንያታዊነትና ሚዛናዊነት ይልቅ ስሜታዊነት፣ አርበኝነትና “ኧረ ጥራኝ ጫካው፤ኧረ ጥራኝ ዱሩ!” ቅኝት የሚያመዝንባቸው።

በተያያዥ ምልከታ ሊነሳ የሚችለው ሁለተኛው መሠረታዊ ችግር ነፃነትንና ኃላፊነትን (Freedom and Responsibility) ባሰናሰለ መልኩ ሞያውን በመከወን ረገድ የሚስተዋለው ክፍተት ነው። ከዚህ አንፃር አገሪቱ ዉስጥ ያሉትን የግል ሚዲያ ተቋማት በደምሳሳው በሦስት ክፍለን ልናያቸው እንችላለን፡-በመጀመሪያው ረድፍ የምናገኛቸው ነፃነትን በኃላፊነት ኪሳራ (freedom at the expense of responsibility) ማስኬድ የሚፈልጉቱን ሲሆን ሞያው የሚጠይቀውን (የሕዝብ አገልጋይነት፣የጨዋታውን ሕግ የማክበርና የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም የማክበርና የማስጠበቅ) ኃላፊነቶች ለምርጫ የማይቀርቡ ግዴታዎች እንደሆኑ ያለመቀበል ዝንባሌ የሚስተዋልባቸው አሉ። በሁለተኛው ረድፍ የተቀመጡት በነፃነት ኪሳራ ለመንግስት ያላቸውን ታማኝነት (loyalty at the expense of freedom) ለመግለፅ የሚታትሩ ወይም በገዢው ፓርቲ ቋንቋ “ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ያልተቀበሉ ግን ደግሞ ‘ልማታዊ ጋዜጠኝነት’ን ለመተግበር የቆረጡ የሥርዓቱ ተለጣፊዎች” ሲሆኑ እጅግ በጣም ጥቂቶቹን ደግሞ ከነችግሮቻቸው በሦስተኛው ረድፍ ማለትም ኃላፊነትንና ነፃነትን በበቂ ሁኔታም ባይሆን ለማመቻመች ከሚጥሩት ወገን እናገኛቸዋለን። ከዚህ ከሦስተኛው በስተቀር ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ  በየአሰላለፋቸው የፖለቲካዊ “አክቲቪዝም” አገልጋዮች ሆነው እናገኛቸዋለን።

በኔ ዕይታ ሦስተኛዉና የመጨረሻው ነጥብ ጋዜጠኝነት የሚጠይቀዉን ሞያዊ እዉቀትና ክህሎት ይመለከታል። በዚህ ረገድ ለአክቲቪዝም የሞያ ዘርፍ እንደ ጥሬ እቃ የሚያገለግሉት ግብዓቶች ማለትም፤ የጋለ የፖለቲካ ስሜት ፣ የእናት ሀገር ፍቅር፣ የግልና የቡድን ቂም፣ አርበኝነትና ደረቅ ወኔ ወዘተ ‘ለበጎ’ ዓላማ እስከዋለ ድረስ እንደ ጥሩ እሴቶች ቢወሰዱም እንኳን ለጋዜጠኝነት የሞያ ዘርፍ ዋነኛ ግብዓቶች የመሆናቸው አገባብ ሊኖር አይገባም እላለሁ።

## የመፍትሔ ሃሳቦች፡-

### የፕሬስ ካውንስል፡-

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እውን ሊሆን የሚችለው በተራዘመ ሂደት ውስጥ እንደሆነው ሁሉ የዳበረ የሚዲያ ባህል የመፍጠር እውነታም በዚሁ ረጅም ጉዞ ማለፉ የግድ ይሆናል። በዚህ ረገድ የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ባህል ባልነበራቸውና በሂደት መፍጠር ከቻሉት እንደ ጋና አይነቱ አፍሪካዊት ሀገር መውሰድ የምንችለው ጠቃሚ ተሞክሮ ቢኖር ለምክንያታዊና አሳታፊ የሚዲያ ባህል መፈጠር ገለልተኛ የፕሬስ ካውንስል ተቋም የሚኖረው ሚና ከፍተኛ የመሆኑን እውነት ነው።

ከመንግስት፣ ከግሉ ሚዲያ ዘርፍና ከሌሎች ገለልተኛ ከሆኑ ሞያተኞችና የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚዋቀረው የፕሬስ ካውንስል ዋነኛ ተግባር የሚሆነው ፕሬሱ እርስ በርስ የሚወያይበትን፣የሚገማገምበትንና ዘርፉ ራሱን የሚያርምበትንና ጠንካራ ጎኖቹን እያዳበረ እንዲሁም ክፍተቶቹን እየሞላ የሚሄድበትንና የሞያ ክህሎት፣የእውቀትና የስነምግባር መስተጋብሮች በተገቢው መጠንና በሕጉ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚሠሩበትን መድረክ (self-governing system) መፍጠር ነው። ጎን ለጎንም የፕሬስ ካውንስሉ በዘርፉ የሚታየውን የሞያ እውቀትና የክህሎት ክፍተቶችን ለሞሙላት አስፈላጊ ሥልጠናዎችን በማመቻቸት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን የሚያከናዉን ይሆናል።

የገለልተኛ ፕሬስ ኮሚሽን መፈጠር ለሀገራችን ያለዉን አስፈላጊነት በቀላሉ ለመረዳት መንግስት በተወሰኑ የግል የሕትመት ዉጤቶች ላይ ሰሞኑን እየወሰደ ያለዉን የክስ እርምጃ መመልከቱ በቂ ነው። አገራችን ዉስጥ ያለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመፍጠር ሁነት ገና ሂደት ላይ ያለ እውነታ እንደመሆኑ የዴሞክራሲ ተቋማቱ (ሚዲያን ጨምሮ) ገለልተኛ በሆነ የሞያና የሥነምግባር ተቋማት ዘንድ የእርስ በርስ የመገማገሚያና የመተራረም ዴሞክራሲያዊ ባህል እየፈጠሩ የሚመጡበትን ዕድል ከማዳበር ይልቅ መንግስት በሞያዊ አቅም፣ በገንዘብና ቁሳዊ አቅም ውስንነት እየተንገዳገዱ ያሉትን እንዲሁም ከ 80 ሚሊዮን ሕዝብ መሃል እዚህ ግባ የማይባል የሕዝብ ተደራሽነት ያላቸውን የግል የሕትመት ዉጤቶች አሳማኝነታቸው አከራካሪ በሆኑ የስጋት ምንጭ መነሻነት ፍርድ ቤት ማቆሙ የዳበረ የሚዲያ ባህል ለመፍጠር ገና ሂደት ላይ ባለች አገር ዉስጥ

መፍትሔ መሆኑ ቀርቶ ጅምር ላይ ላለው የፕሬስ ኢንዱስትሪ የህሊና ፀሎት ለማድረግ እንዳንገደድ በግሌ የተሰማኝን ስጋት ከወዲሁ መግለጽ እሻለሁ።

**የቢቢሲው ሞዴል፦**

ይህ ንዑስ ርዕስ የሚያተኩረው የመንግስት ሚዲያን እንዴት ወደ አሳታፊ፣ምክንያታዊና ብሎም የሕዝብ አገልጋይ የሚዲያ ተቋም ማሳደግ ይቻላል በሚለው የሃሳብ መነሻ ነው። በዚህ ረገድ መንግስት የተቋሙን ቅርፅ በኮርፖሬሽን መልክ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ማለትም (የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን) በሚል ሰሞኑን ያጸደቀውን አዋጅ እንደ በጎ የለውጥ እንቅስቃሴ እየቆጠርኩኝ ለውጡ ከስማዊ ለውጥ በዘለለ ተጨባጭ መዋቅራዊ ትራንስፎርሜሽን ያመጣ ዘንድ ግድ በሚሉ ተያያዥ ተግባራዊ እርምጃዎች ላይ አተኩራለሁ።

እዚህ ላይ የቢ.ቢ.ሲን ሚዲያ ተቋም የአወቃቀር ሞዴል በማጤን ጠቃሚ ተሞክሮዎችን ማንሳት ይቻላል። ቢ.ቢ.ሲ ከግብር ከፋዩ የሕብረተሰብ ክፍል በሚሰበሰብ ገቢ የመንቀሳቀሱን ያህል በኢኮኖሚው ረገድ የመንግስት ጥገኛ ሆኖ እያለ ከፖለቲካው አንጻር ራሱን የቻለና ከመንግስት ነጻ የሆነ የሚዲያ ተቋም ይሆን ዘንድ ያስቻሉትን የተቋሙን መዋቅራዊ አደረጃጀቶች መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

በቢ.ቢ.ሲ ተቋማዊ አደረጃጀት ዉስጥ ሦስት የመዋቅር ክፍሎች ይገኛሉ፦ቢ.ቢ.ሲ ትረስት፣ ኤክስኪዩቲቭ ቦርድና የአድማጭ ካውንስል ናቸው።የቢ.ቢ.ሲ ትረስት በዋና ዋና የሃገሪቱና የመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የማስቀመጥ ግዴታ ያለው ሲሆን ይህንኑ ለ ኤክስኪዩቲቭ ቦርዱ የሚያቀርብ ይሆናል። በነገራችን ላይ ኤክስኪዩቲቭ ቦርዱ ሙሉ በሙሉ ከመንግስት ቀጥተኛ ውክልና ነጻ የሆነና በራሱ የቢ.ቢ.ሲ ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ባለሞያዎች የተዋቀረ ነጻ የባለሞያዎች ስብስብ ዉጤት ነው። በመሆኑም የተቋሙ ጠቅላላ የሥራ አመራር አተገባበር(operational management) ሙሉ በሙሉ በዚሁ ነጻና ገለልተኛ ኤክስኪዩቲቭ ቦርድ ይከወናሉ።ከኤክስኪዩቲቭ ቦርዱ ስር የምናገኘው የመጨረሻው አካል የአድማጭ ካውንስልን ነው። ይህ የአድማጭ ካውንስል በራስ ተነሳሽነትና ፈቃድ በሚውጣጡ ገለልተኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚዋቀር ሲሆን ዋነኛ ተግባሩም የጥናትና

የዳሰሳ ምልከታዎችን በማካሄድ  የሕዝቡን ጥቅም፣ፍላጎትና ምርጫን ለኤክስኪዩቲቭ ቦርዱ ማቅረብ ይሆናል።

ሰሞኑን መንግስት ተቋሙን በአዲስ መልክ ለማደራጀት የወሰደውን እርምጃ እንደበጎ የለውጥ እንቅስቃሴ ስንወስድ ይህን የቢ.ቢ.ሲ.ንና መሰል ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ አገራችን ዉስጥ ባለው የመንግስት ሚዲያ ተቋም የሚኖረውን የዕለት ተዕለት የሥራ አመራር ሂደትን በተለይ በተለይ ነጻና ገለልተኛ በሆነው የባለሞያዎች ቦርድ በበላይነት እንዲመራና እንዲከወን በማድረግ ረገድ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነትና ተግባራዊ እርምጃዎች ከመንግስት የሚጠበቁ መሆናቸውን በማሳሰብ ጭምር ነው።